ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 4 ላይ
**ድምጽዎን ለ ዴሞክትራቶች ይስጡ**

**የመለው ግዛት እጩ ተወዳዳሪዎች**

**የአርሊንግተን ተወዳዳሪዎች**

**በ ድምጽ መስጫዎ ላይ የሚገኙ ዴሞክራቶች**
**የቨርጂንያ ጉዳዮችን ማሳካት**

- ለሁሉም የአርሊንግተን ማህበረሰቦች መብት መከበር መቆም
- የጤና እንክብካቤ፣ የመኖሪያ በኢት እና የሀይል ክፍያዎችን መቀነስ
- የፌደራል ሰራተኞችን እና ኮንትራክተሮችን መብት መጠበቅ
- የህዝብ ትምህርት ቤቶቻችንን ማጠናከር
- የቤተሰቦቻችንን ደህንነት መጠበቅ

**Abigail Spanberger**
ገዢ

Abigail ቨርጂኒያን ለመኖር እና ቤተሰብ ለማፍራት የሚቻልባት ለኑሮ ተመጣጣኝ የሆነች ከተማ ለማድረግ ለከተማዋ ገዢነት በምርጫ እየተወዳደረች ነው። ያደገችው በሪችመንድ አቅራቢያ መካከለኛ ገቢ ያለው ቤተሰብ ውስጥ ሆኖ እና የስራ ህይወትዋን የጀመረችው በ ፌደራል ህግ አስከባሪነት፣ ህጻናት አዳኞችን በመመርመር እና በናርኮቲክ ጉዳዮች ላይ በመስራት ነው።

እንደ አንድ የኮንግረስ አባል፣ Abigail ምንም እንኳን ፈተናዎች ቢኖሩም፣ በሁለቱም በትራምፕ እና በባይደን አስተዳደሮች ውጤቶች ማምጣት የቻለች እና ከቨርጂኒያ ከሁለቱ ወገን ጋር አብራ በመስራት ምርጥ የኮንግረስ አባል ሆናም ተመርጣለች።

**Ghazala Hashmi**
ሌተናንት/ምክትል ገዢ

Ghazala Hashmi ወደ 30 አመት የሚጠጋ ልምድ ያላት አስተማሪ፣ እናት እና የግዛት ሴናተርነት ስራዋን ለቨርጂኒያውያን በመታገል ያሳለፈች ናት።

እንደ አንድ የግዛት ሴናተር፣Ghazala የመንግስት ትምህርት ቤቶቻችን ሙሉ በሙሉ የገንዘብ ድጋፍ እንዲደረግላቸው፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ለመጠበቅ እና የመራቢያ መብቶቻችንን እንዲጠበቁ ለማድረግ ግፊት ስታደርግ ቆይታለች።

**Jay Jones**
ጠቅላይ አቃቤ ህግ

የኖርፎልክ የዕድሜ ልክ ነዋሪ እና የሁለት ወንድ ልጆች አባት የሆነውJay Jones፣ የቀድሞ ረዳት ጠቅላይ አቃቤ ህግ እና የቀድሞ የተወካዮች ምክር ቤት አባል ነው።

Jay የቤተሰብን ደህንነት ለመጠበቅ ለመሳሪያ ይዞታ የሚደረግ ድጋፍን ታግሏል፣ ኮርፖሬሽኖቹ የግሮሰሪ ዋጋ እንዳይጨምሩ ተከላክሏል እንደዚሁም ትልልቅ ባንኮች እና ስግብግብ አከራዮች ለድርጊታቸው መልስ እንዲሰጡ አድርጓል።

## Patrick Hope

የተወካዮች ምክር ቤት፣ ዲስትሪክት 1

ከ 2009 ጀምሮ የ ቨርጂኒያ 1ኛ ዲስትሪክት ተወካይ የነበረው Patrick Hope፣ ለዘጠነኛ የስልጣን ዘመን በድጋሚ የምርጫ እጩ ሆኖ እየተወዳደረ ነው። በ ህግ አውጪነት የስራ ዘመኑ ግዜ፣ Patrick ከ 115 በላይ የሆኑ ቢሎች ህግ ሆነው እንዲጸድቁ ያደረገ እና ለ ጤና እንክብካቤ፣ ሲቪላዊ መብቶች እና በመሳሪያ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከል ላይ ድጋፍ ሰጥቶ ሰርቷል። Patrick አርሊንግተንን በማገልገል ኩራት የሚሰማው ሲሆን ያለውን ልምድ እና ውጤታማነቱን ተጠቅሞ የሲቪል መብቶችን ለመጠበቅ እና ሁሉም ሰው ደህንነቱ የተጠበቀበት፣ ይበልጥ ጤናማ የሆነ የጋራ ሃብትን ለመፍጠር የእርስዎን ድጋፍ ይጠይቃል።

## Adele McClure

የተወካዮች ምክር ቤት፣ ዲስትሪክት 2

Adele McClure የመኖሪያ ቤት እና የህጻናት እንክብካቤ አገልግሎት ክፍያ ተመጣጣኝነትን፣ በመሳሪያ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን መከላከልን፣ የመራቢያ ነጻናትን እና ሌሎችንም ነገሮች በቀጣይነት ለመደገፍ ለድጋሚ ምርጫ በመወዳደር ላይ ትገኛለች። መብቶችን የሚያስፋፉ፣ መሰናክሎችን  የሚያስወግዱ እና በ አርሊንግተን በመላው የኮመንዌልዝ አከባቢ ውስጥ ወሳኝ አገልግሎቶች ተደራሽነትን የሚያጠናክሩ ተጽእኖ ፈጣሪ ህጎችን ለማስጸደቅ ከባለድርሻ አካላት፣ ከመብት ተማጓቾች፣ ከማህበረሰብ መሪዎች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዛ ትሰራለች።

## Alfonso Lopez

የተወካዮች ምክር ቤት፣ ዲስትሪክት 3

Alfonso Lopez ትምህርትን፣ የአከባቢ ጥበቃ፣ የመኖሪያ ቤት ዋጋ ተመጣጣኝነት፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን እና እንግዳ ተቀባይ የሆነ ማህበረሰብ መገንባትን ጨምሮ፣ ለአርሊንግተን ነዋሪዎች ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከ 30 ዓመት በላይ የህግ አውጪነት ልምድ ያለው ነው። የቀድሞ የ Obama አስተዳደር የፖለቲካ ተሿሚ፣ የ Kaine አስተዳደር የካቢኔ ተሿሚ እና የምክር ቤቱ የዲሞክራቲክ ካውከስ (አንድ የፖለቲካ ፓርቲ እንደ ቡድን እጩዎችን የሚመርጥበት ዝግ ስብሰባ) የፓርቲ ዲሲፕሊን አስፈፃሚ የነበረ ሲሆን፣ ማንንም ወደ ኋላ ሳይተው ሁሉንም ከፍ የሚያደርግ ቨርጂኒያን ለመገንባት በየቀኑ ይታገላል።

## Takis Karantonis

የአርሊንግተን ካውንቲ ቦርድ

Takis Karantonis በ ካውንቲው ቦርድ ላይ የአርሊንግተን ነዋሪዎችን ማገልገሉን ለመቀጠል በድጋሚ ለምርጫ በመወዳደር ላይ ይገኛል። ስደተኞችን እና የፌደራል ሰራተኞችን አምባገነን ከሆነ የአስተዳደር ስርዓት ለመጠበቅ ይታገላል። የቤት ችግርን መጋፈጥ፣ ኢኮኖሚያዊ ፍትህን ማሳደግ፣ የአየር ንብረት እርምጃ፣ ህዝባዊ ትምህርት፣ ተጠያቂነት ያለው አስተዳደር እና ጠንካራ የማህበራዊ ደህንነት

መረብ ላይ ትኩረት አድርጎ ይሰራል። ከምንም በላይ ግን ሁሉም ነዋሪዋ ቤቴ ብሎ ለመጥራት የሚኮራባት፣ ዴሞክራሲያዊት፣ ፍትሃዊት እና ሁሉን አቃፊ የሆነችን አርሊንግተን ለመፍጠር ቁርጠኛ ነው።

**Monique “Moe” Bryant**
የአርሊንግተን የትምህርት ቤት ቦርድ

የ 13 ዓመት የ APS ተማሪ የሆነ ልጅ ወላጅ፣ የአርሊንግተን ለትርፍ የማይሰራ ድርጅት መሪ የሆነችው “Moe” Bryant፣ የተመሰከረላት የ ትምህርት ቤቶች እና የማህበረሰብ የመብት ተሟጋች ናት። Moe APS ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞቹ እና ለማህበረሰቡ የተመረጠ ለማድረግ አዛኝነት እና ተሳትፎ ማዕከል አድርጎ ስራ መሰራቱን ታረጋግጣለች። 2024 APS የትምህርት ቤት ቦንድ ዘመቻን በ ምክትል ሊቀመንበርነት የመራች ሲሆን፣ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥም የበጎ ፈቃድ ስራዎችን ሰርታለች። በአንዳንድ የሀገራችን ከባድ ጉዳዮች ላይ የመግባቢያ ድልድይ በመገንባት የሚታወቀው፣ የ Challenging Racism ዋና ዳይሬክተር ናት።

## ድምጽዎን ለመስጠት እስከ ኦክተበር 24 ይመዝገቡ

**<u>አስቀድሞ በ አካል ድምጽ መስጠት</u>**

ሴፕቴምበር 19 – ኖቬምበር 1፣ 2025

**Courthouse Plaza, Office of Elections, Suite 320**

ዘወትር በሳምንቱ ቀናት፣ ሴፕቴምበር 19 – ኦክተበር 31፣ 8am–5pm

ዘወትር ማክሰኞ፣ ሮብ እና ሓሙስ ኦክተበር 21-23 & ኦክተበር 28-30፣ 8am–7pm

**<u>ኦተበር 21 ላይ የሚኖሩ ተጨማሪ የስራ ሰዓቶች እና ቦታዎች</u>**

**Courthouse Plaza, Madison Community Center,**
**& Walter Reed Community Center**

ቅዳሜ ኦክተበር 25 እና ኖቬምበር 1፣ 9am–5pm | እሁድ ኦክተበር 26፣ 11am–3pm

ዘወትር ማክሰኞ፣ ሮብ እና ሓሙስ ኦክተበር 21-23 & ኦክተበር 28-30፣ 2-7pm

**<u>በ ፖስታ ድምጽን መስጠት</u>**

**እስከ ኦክተበር 24 5pm ድረስ የፖስታ ድምጽ መስጫ እንዲላክልዎ ይጠይቁ**

**<u>የፖስታ ድምጽ መስጫዎን በ ፖስታ መልሶ መላክ፥</u>**

ፖስታው እስከ ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 4 ድረስ ፖስት ማርክ ተደርጎ እስከ ዓርብ ኖቬምበር 12pm ሊደርሰን ይገባል። **በተቻለ መጠን ፈጥነው መልሰው ይላኩልን-ፖስታ የማድረስ ሂደቱ 10 ቀናትን ሊፈጅ ይችላል።**

**<u>የድምጽ መስጫዎን በአካል በሚከተሉት ቦታዎች ላይ በመገኘት ይመልሱ፥</u>**

- እስከ ኖቬምበር 4 7pm በማናቸውም ድምጽ መስጫ ጣብያዎች
- ከ ኖቬምበር 4 በፊት  የቅድመ ድምጽ መስጫ  ቦታዎች ላይ
- እስከ ኖቬምበር 4 7pm በማናቸውም 24/7 drop box (ድሮፕ ቦክስ) ላይ

**<u>የድምጽ ሰጪ መለያ ቁጥር፧</u>**

ማናቸውም ድምጽ ሰጪዎች ድምጽ ለመስጠት ሲመጡ ተቀባይነት ያለው የማንነት መለያ ሊያሳዩ ይገባል ወይም የማንነት ማረጋገጫ መግለጫ ላይ ሊፈርሙ ይገባል።

www.elections/virginia/gov

**<u>የምርጫ ቅደም ተከተል ድምጽ አሰጣጥ</u>**

**Takis Karantonis ን በ ድምጽ መስጫዎ ላይ 1ኛ ደረጃ ይስጡ።**

የምርጫ ቅደም ተከተል ድምጽ አሰጣጥ በ ካውንቲው የ ቦርድ ምርጫ ላይ ብቻ ነው ጥቅም ላይ የሚውለው።

**<u>ወደ ድምጽ መስጫ ቦታው ለመሄድ የመጓጓዣ አገልግሎት ይፈልጋሉ?</u>**

በ 703-528-8588

info@arlingtondemocrats.org ተጠቅመው ያግኙን

**ድምጽዎን ለመስጠት ዕቅድ ይያዙ።  በአካል ቀርበው አስቀድመው ወይም በፖስታ ተጠቅመው ድምጽዎን መስጥት ይችላሉ። አሁናዊ አድራሻዎ ላይ መመዝገብዎን እርግጠኛ ይሁኑ። የምርጫ ቀን ኖቬምበር 4 መሆኑን ያስታውሱ።**